# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

# የመንግስት ንብረትን ለማስወገድ የሚውል መደበኛ የጨረታ ሰነድ

አዲስ አበባ
ጥር/2010 ዓ.ም

**መቅድም**

ማንኛውም የፌደራል መንግስት ተቋማት ንብረቶችን በሽያጭ ማስወገድ የሚችለው በመንግስት የግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ፣ በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 እንዲሁም ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በተዘጋጀው በዚሁ መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት ይሆናል፡፡

ይህ መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተዘጋጀ ሲሆን ዓላማውም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሲገለገሉባቸው የቆዩ አላቂ እና ቋሚ ንብረቶችን በሽያጭ ለማስወገድ በሚወስኑበት ጊዜ በዋነኛነት በገዥና በሻጭ መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን በቀላሉ ለመፍታት እንዲያስችል ፣ የአወጋገድ ስርዓቱ ግልፅ እና ከአድሎ የነፃ እንዲሆን ፣ ፍትኃዊ የንብረት አወጋገድ ሥርዓት እንዲሰፍን ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

# ማ ው ጫ

**ተ.ቁ.** **ርዕስ** **ገጽ**


ክፍል 1 **ተጫራቾች ስለመጋበዝ**......1

በሀራጅ ስለሚደረግ ሽያጭ......1

1.2 በግልፅ ጨረታ ስለሚደረግ ሽያጭ......1

ክፍል 2 **የተጫራቾች መመሪያ**......2

2.1 ስለ ተጫራቾች ብቃት ወይም ከተጫራቾች ስለሚጠበቅ ሁኔታ፤......2

2.2 ከጨረታው ጋር ተያይዞ ስላሉ ወጪዎች፤......2

2.3 የጨረታ ሰነድ፤......2

2.4 በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለሚሰጥ ማብራሪያ፤......3

2.5 የጨረታ ሰነድ ስለማስተካከል፤......3

2.6.የጨረታ መነሻ ዋጋ፤......3

2.7 የጨረታ ማስከበሪያ ፤......4

2.8የውል ማስከበሪያ......4

2.9 ጨረታ ፀንቶ ስለሚቆይበት ሁኔታ፤......4

2.10. ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ለተጫራቾች ስለማሳየት፤......5

2.11. ስለ ዋጋ አቀራረብ፤......5

2.12 የዋጋ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን፤......6

2.13.የጨረታ ሰነድ ስለማስተካከል፤......6

2.14ከጨረታ ስለመውጣት፤......6

2.15 ስለጨረታ አከፋፈት፤......7

2.16 ጨረታ ግምገማና ውድድር፤......7

2.17 አሸናፊውን የማሳወቂያ መስፈርት፤......8

2.18 አሸናፊውን ስለማሳወቅ፤......8

2.19ከሻጭ መስሪያ ቤት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት፤......8

ክፍል 3 **አጭበርባሪነት፣ሙስና እና አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት**......9

3.1 የማጭበርበርና የሙስና ድርጊት......9

3.2 አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት......9

ክፍል 4. **የጨረታ ማቅረቢያ እና የውል ስምምነት ቅፆች**......10

4.1. የጨረታ ማቅረቢያ ቅፅ......10

4.2. የፍላጎት መግለጫ ........................................................................................................................ 11
4.3 የውል ስምምነት ቅፅ ........................................................................................................................ 12

## ክፍል 1 ተጫራቾች ስለመጋበዝ

### በሀራጅ ስለሚደረግ ሽያጭ

የመንግስት መ¼ቤቶች ንብረቶቻቸውን በሃራጅ ለማስወገድ ሲወስኑ በሀራጅ ማስታወቂያቸው ላይ ቀጥሎ የተመለከቱትን ዝርዝሮች ማካተት አለባቸው፡፡

i. የመንግስት መ/ቤቱን ስምና አድራሻ፣
ii. የዕቃዎች ብዛት እና አይነት በሚመለከት አጠቃላይ መግለጫ፣
iii. እቃዎች የሚገኙበት ቦታ፣
iv. የእቃዎች ዝርዝር የሚገኙበትን ቦታ ፣
v. የሀራጅ ሽያጭ የሚከናዎንበት ቦታና ቀን፣
vi. ክፍያ ሚፈፀምበትን ጊዜ፣
vii. የመንግስት መ/ቤቱ ማናቸውንም ጨረታ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል የሚችል መሆኑን እና በማናቸውም ጊዜ ሊሰርዘው እንደሚችል የሚገልፅ ሐረግ፣

### 1.2 በግልፅ ጨረታ ስለሚደረግ ሽያጭ

የመንግስት መ/ቤቶች ንብረቶቻቸውን በጨረታ ለማስወገድ ሲወስኑ ማስታወቂያቸው ላይ ቀጥሎ የተመለከቱትን ዝርዝሮች ማካተት አለባቸው፡፡

i. የመንግስት መ/ቤቱን ስምና አድራሻ፣
ii. የእቃዎችን አይነትና ብዛት በሚመለከት አጠቃላይ መግለጫ
iii. ዕቃዎች ወይም ንብረቱ የሚኙበትን ቦታ፣
iv. የእቃዎችን ወይም የንብረቱን ዝርዝር ከየት ማግኘት እንደሚቻል፣
v. ጨረታዎች መቅረብ የሚችሉበት የመጨረሻ ቀን
vi. የጨረታ ሳጥኑ የሚገኝበትና የሚዘጋበት ትክክለኛ ቀንና ጊዜ ፣
vii. ጨረታዎች የሚከፈቱበት ቀን ፤ ቦታ እና ሰዓት፣
viii. የጨረታ ማስከበሪያውን መጠንና ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ከውድድሩ ቢወጡ የጨረታ ማስከበሪያውን ለመንግስት ገቢ እንደሚሆን የሚገልፅ ሀረግ ፣
ix. የጨረታ አሸናፊው ክፍያውን የሚፈፅምበት ጊዜ፤

x. የጨረታ አሸናፊው ክፍያውን ፈፅሞ ንብረቱን ሙሉ በሙሉ የሚያነሳበት ጊዜ መገለጽ አለበት፣

xi. የመንግስት መ/ቤቱ ማናቸውንም ጨረታ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል እንደሚችልና በቂ ምክንያት ሲኖረው በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን እንደሚሰርዝ፣

xii. ተጫራቾች እንዲጫረቱ የሚሰጠው ጊዜ በ15 እና በ30 ባሉት ቀናት መካከል ሆኖ በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የሚወሰን ይሆናል፣

xiii. የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት ዋጋና የተሟላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና/ሲፒኦ/ መሆኑ ፣

## ክፍል 2 የተጫራቾች መመሪያ

### 2.1 ስለ ተጫራቾች ብቃት ወይም ከተጫራቾች ስለሚጠበቅ ሁኔታ፤

2.1.1 ይህ ጨረታ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው / ያላት /ሊሳተፍበት ይችላል።

### 2.2 ከጨረታው ጋር ተያይዞ ስላሉ ወጪዎች፤

2.1.2 ማንኛውም ከጨረታው ጋር ተያያዥ የሆኑ ወጪዎች ለምሳሌ፡ የማስታወቂያ ወጪ ፣ የፅህፈት መሳሪያ ወጪ፣ የሠራተኞች አበል የመሳሰሉት በሻጭ መስሪያ ቤት የሚሸፈኑ ይሆናል።

2.1.3 የጨረታ ሠነድ መሸጫ ዋጋ በሻጭ መስሪያ ቤት የሚወሰን ሆኖ ሻጭ መስሪያ ቤት ከጨረታው ጋር ተያይዞ ለወረቀትና ለቀለም የሚያወጣውን ወጪ መተኪያ ሊጠይቅ ይችላል።

2.1.4 የሚወገደው ንብረት ተሽከርካሪ ወይም ማሽኖች ከሆኑ በወቅቱ ያልተከፈለ የቀረጥ እና የቦሎ ወጪ ካለ የንብረቱ ባለቤት ወይም ንብረቱን ሲገለገልበት በነበረው መ/ቤት የሚሸፈን ይሆናል።

2.1.5 ሌሎች ወጪዎች ማለትም የስም ማዛወሪያ ፣ የትራንዚት ወጪ ወዘተ… የመሳሰሉት በገዥው የሚሸፈን ይሆናል።

### 2.3 የጨረታ ሰነድ፤

2.3.1 የጨረታ ሰነዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁሉ ሊያሟላ ይገባል፤

I. ጨረታው በማስታወቂያ ስለመጠራቱ

II. ስለተጫራቾች መመሪያ፣

III. የሚወገዱ ንብረቶች አይነትና የጨረታ መነሻ ዋጋ፣

IV. ከተጫራቾች ስለሚጠበቅ ሁኔታ፤

V. ለጨረታ የሚያስፈልጉ ቅፃችን፤

VI. ሚስጥራዊ የዋጋ ማቅረቢያ ቅፃችን፤

VII. በገዥ እና በሻጭ መካከል ስለሚኖር መብትና ግዴታ፤

## 2.4 በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለሚሰጥ ማብራሪያ፤

2.4.1 ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ሰነዱ ላይ ሊብራራለት የሚፈልገው ነገር በሚኖርበት ጊዜ ጨረታው ከመዘጋቱ 5 ቀን በፊት በጽሁፍ ሻጭ መስሪያ ቤትን መጠየቅ የሚችል ሲሆን ሻጭ መስሪያ ቤትም በእርግጥም ማብራሪያ ያስፈልገዋል ብሎ ሲያምን የተስተካከለውን ማብራሪያ ሁሉም ተጫራቾች እንዲያውቁት በመስሪያ ቤቱ የማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

## 2.5 የጨረታ ሰነድ ስለማስተካከል፤

2.5.1 ሻጭ መስሪያ ቤት የጨረታ ሰነዱ መስተካከል አለበት ብሎ ሲያምን ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ የጨረታ ሰነዱን ማስተካከል ይችላል፡፡

2.5.2 ሻጭ መስሪያ ቤት የተስተካከለውን የጨረታ ሰነድ ሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪወዎች መጥተው እንዲወስዱ በመ/ቤቱ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

2.5.3 ሻጭ መስሪያ ቤት የተስተካከለውን የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች በድጋሚ በሚሰጥበት ጊዜ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን አንብበው የመጫረቻ ሰነዳቸውን እንዲያቀርቡ በቂ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## 2.6 የጨረታ መነሻ ዋጋ፤

2.5.4 ሻጭ መስሪያ ቤት ስለእያንዳንዱ ሊወገድ ስለቀረበ ዕቃ ዓይነት ፣ የነጠላ የጨረታ መነሻ ዋጋ በግልፅ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመላከት አለበት፡፡

2.5.5 ተጫራቾች በተቀመጠው መነሻ ዋጋ እና ከዚያ በላይ በሆነ ዋጋ ብቻ መወዳደር ያለባቸው ሲሆን ከተቀመጠው የጨረታ መነሻ ዋጋ በታች ቢያቀርቡ ከጨረታ ውድቅ መደረግ አለባቸው፡፡

2.5.6 በጨረታው ላይ የሚሳተፉት ኢትዮጵውያን ብቻ በመሆናቸው የኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ በሻጭ እና በገዥ መካካል ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 2.7 የጨረታ ማስከበሪያ ፤

2.7.1 ማናቸውም ተጫራች ሻጭ መስሪያ ቤት ያስቀመጠውን መጠን ያህል የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ( ሲ ፒ ኦ ) ማስያዝ ይኖርበታል፡፡

2.7.2 ማናቸውም ተጫራች ጨረታው ከተዘጋ በኂላ በራሱ ፈቃድ ከጨረታው ቢወጣ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘው ገንዘብ ተወርሶ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

2.7.3 ማናቸውም ተጫራች ከተጫረተ በኂላ በሌሎች ተጫራቾች ተበልጦ ቢሸነፍ ከ5 የሥራ ቀናት በኂላ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘው ገንዘብ ይመለስለታል፡፡

## 2.8 የውል ማስከበሪያ

2.8.1 ማናቸውም ተጫራች ተጫርቶ ያሸነፈ እንደሆነ ያሸነፈባቸውን ዕቃዎች ሙሉ ክፍያ ከፍሎ እስከሚወስድ ድረስ ለውል አተገባበር ዋስትና የሚሆን የጠቅላላ ዋጋውን 10 በመቶ በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ አለበት፡፡

2.8.2 ማናቸውም ተጫራች ሌሎች አሰገዳጅ ሁኔታዎች እስካልተፈጠሩ ድረስ ተጫርቶ ያሸነፈበትን ዕቃ ሙሉ ክፍያ ከፍሎ በ10(አስር) ተከታታይ ቀናት ወስጥ ማንሳት አለበት፣

2.8.3 ሆኖም ተጫራቹ ላሸነፈበት ዕቃ ሙሉ ክፍያ ከፍሎ ነገር ግን ዕቃውን በ10(አስር) ቀናት ውስጥ ካላነሳ ከ10ኛው ቀን በኂላ ላላነሳበት ቀን በየቀኑ ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ ቅጣት መክፈል አለበት፡፡

2.8.4 ከላይ በተራ ቁጥር 2.8.3 የተገለፀው ካልሆነ ተጫራቹ ተጫርቶ ያሸነፈበትን ዕቃ እንደማይፈልገው ተቆጥሮ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ንብረቱ ተወርሶ እንደገና ለህዝብ በጨረታ ይሸጣል፡፡

## 2.9 ጨረታ ፀንቶ ስለሚቆይበት ሁኔታ፤

2.9.1 ጨረታው አየር ላይ የሚቆይበት ጊዜ በሻጭ መስሪያ ቤት የሚወሰን ሆኖ ጨረታው ከተዘጋ በኂላ የሚመጣ የዋጋ ማቅረቢያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2.9.2 ጨረታው አየር ላይ የሚቆይበትን ጊዜ ሻጭ መስሪያ ቤት እንደአስፈላጊነቱ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

## 2.10. ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ለተጫራቾች ስለማሳየት፤

2.10.1 ባለ ንብረት መስሪያ ቤት ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ጨረታው እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ለተጫራቾች በግልፅ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

## 2.11. ስለ ዋጋ አቀራረብ፤

2.11.1 ማንኛውም ተጫራች የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዱን በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ ውስጥ በማድረግ ሻጭ መስሪያ ቤት ባዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ወይም በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የዋጋ ማቅረቢያ እንዲቀበል ኃላፊነት ለተሠጠው ሰራተኛ ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

2.11.2 ማንኛውም ተጫራች ሌሎች ተጫራቾች በሰጡት ዋጋ ላይ በመንተራስ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡

2.11.3 ተጫራቾች የሚያቀርቡት አንድ ዋና (original)እና ቅጂ( copy) የጨረታ ሰነድ ለየብቻው በፖስታ ታሽጎና እንደገና ሁሉም በአንድ ፖስታ ውስጥ ተካቶ የታሸገ መሆን አለበት፡፡ በዋናውና በቅጂው መካከል ልዩነት ቢፈጠር ዋናው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

2.11.4 ተጫራቹ በሚያቀርበው የጨረታ ሰነድ ላይ ስርዝ ድልዝ መኖር የለበትም፡፡ ካለም በፊርማው ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህንን ችግር ከመቅረፍ አንፃር ተጫራቹ ለጨረታ ከወጡ ንብረቶች መካከል ተጫርቶ ለመግዛት የሚፈልገውን ንብረት የነጠላ ዋጋ በአሃዝ እና በፊደል በማያሻማ እና ግልፅ በሆነ ሁኔታ መጫረቻ ሰነዱ ላይ ጽፎ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2.11.5 ተጫራቹ ያቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ ሲታይ ግልፅነት የጎደለው እና የሚያሻማ ሆን ተብሎ ለማጭበርበር ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ሻጭ መስሪያ ቤት ካረጋገጠ የተጫራቹን ዋጋ ማቅረቢያ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.11.6 ማንኛውም ተጫራች በሚያቀርበው የመጫረቻ ሰነድ ግርጌ መፈረም ይኖርበታል፡፡ በተጫራቹ ወይም በተጫራቹ ህጋዊ ወኪል ያልተፈረመበት የመጫረቻ ሰነድ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውድቅ ይደረጋል፡፡

## 2.12 የዋጋ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን፤

2.12.1 ሻጭ መስሪያ ቤት ጨረታው የሚዘጋበትን ቀን እና ሠዓት እንዲሁም የጨረታ ሥነ-ስርዓት የሚደረግበትን ቦታ በጨረታ ሰነዱ ላይ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

2.12.2 ሻጭ መስሪያ ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ጨረታው የሚዘጋበትን ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡ ሆኖም ለሁሉም ተጫራቾች ጨረታው የሚዘጋበት ጊዜ የተራዘመ ስለመሆኑ በመስሪያ ቤቱ ማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ በመለጠፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 2.13 የጨረታ ሰነድ ስለማስተካከል፤

2.13.1 ማናቸውም ተጫራች ዕቃውን ለመግዛት ያቀረበውን ዋጋ ማስተካከል ቢፈልግ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት ለዚሁ ተብሎ ከጨረታ ሰነዱ ጋር በቀረበው የዋጋ ማስተካከያ ቅጽ ላይ የተስተካከለውን ዋጋ በመሙላት የተሞላውን የዋጋ ማስተካከያ በፖስታ በማሸግ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

2.13.2 ተጫራቹ ማስተካከያ የተደረገበት ፖስታ ላይ የተጫራቹ ስም እና ዋጋ ማቅረቢያው ላይ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት ቀን በአግባቡ ማስቀመጥ አለበት፡፡

2.13.3 ጨረታው ከተዘጋ በኂላ የሚቀርብ ማንኛውም የዋጋ ማስተካከያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## 2.14 ከጨረታ ስለመውጣት፤

2.14.1 ማንኛውም ከጨረታ ለመውጣት የሚፈልግ ተጫራች ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት ከጨረታው ለመውጣት የሚፈልግ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ለሻጭ መስሪያ ቤት በማቅረብ እንዲሁም ይህንኑ ከጨረታው ለመውጣት የሚፈልግበትን ደብዳቤ ለጨረታ ከተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ በማስገባት

ከጨረታው መውጣት ይችላል፡፡ይህም በመሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘው ገንዘብ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይመለስለታል፡፡

2.14.2 ማንኛውም ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ ከጨረታ የመውጣት ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## 2.15 ስለጨረታ አከፋፈት፤

2.15.1 ሻጭ መስሪያ ቤት ጨረታው ይከፈታል ብሎ በወሰነበት ቀንና ሰዓት ተጫራቾችና ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመክፈት ተጫራቾቹ ህጋዊ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረባቸውን እና የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በጨረታ አከፋፈቱ ሥነስርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾችን ስም መመዝገብና በዕለቱ የተገኙ መሆናቸውን በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ መደረግ ይይርበታል፡፡

2.15.2 ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ሻጭ መስሪያ ቤት እያንዳንዱን ፖስታ እየከፈተ የተጫራቹን ስም እና ተጫራቾቹ ለእያንዳንዱ ለተወዳደሩበት ዕቃ ያቀረቡትን የመግዣ ዋጋ በንባብ ማሰማት ይኖርበታል፡፡

2.15.3 ሻጭ መስሪያ ቤት ጨረታው በተከፈተበት ዕለት የተከናወኑ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ቃለ ጉባዔ መያዝ ይኖርበታል፡፡

## 2.16 ጨረታ ግምገማና ውድድር፤

2.16.1 ሻጭ መስሪያ ቤት የቀረቡ የዋጋ ማቅረቢያዎች በአግባቡ በመመልከት ህጋዊ ያልሆኑ ተጫራቾችን ማለትም የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ ያላቀረቡትን ፣ የሚያሻማና ግልፅ ያልሆነ ለማጭበርበር ተግባር የቀረበን የዋጋ ማቅረቢያ በመለየት፣ተጫራቾችን ከጨረታ ማስወጣት ይኖርበታል፡፡

2.16.2 የመስሪያ ቤቱ የጨረታ ኮሚቴ ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ ከ30 ቀን በማይበልጥ ጊዜ አሸናፊና ተሸናፊውን በመለየት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2.16.3 ተጫራቾች ለአንድ ምድብ የተለያዩ ዕቃዎችን በጥቅል እና በነጠላ እኩል ዋጋ በመስጠት አሸናፊ ቢሆኑ እንደገና የዋጋ ማሻሻያ አድርገው

እንዲወዳደሩ በማድረግ የተሻለ ዋጋ የሰጠው አሸናፊ ይሆናል፣ ሆኖም ድጋሚ ተመሳሳይ ዋጋ ከሰጡ አሸናፊው በዕጣ እንዲለይ ይደረጋል።

## 2.17 አሸናፊውን የማሳወቂያ መስፈርት፤

2.17.1 ሻጭ መሰሪያ ቤት ለጨረታ ለቀረቡ ዕቃዎች ከቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ መካከል ትልቅ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች ድርጅት/ግለሰብ/ በአሸናፊነት መምረጥ ይኖርበታል።

## 2.18 አሸናፊውን ስለማሳወቅ፤

2.18.1 ሻጭ መስሪያ ቤት አሸናፊና ተሸናፊውን ከለዩ በኂላ የአሸናፊዎችን ዝርዝር ማስታዎቂያ ሠሌዳ ላይ መለጠፍ አለበት፤

2.18.2 አሸናፊ ተጫራቾች የአሸናፊዎች ዝርዝር ማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከ7(ሰባት) ተከታታይ የስራ ቀናት በኂላ ባሉት 5(አምስት) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ከሻጭ መስሪያ ቤቱ ጋር ውል መፈራረምና የውል መስከበሪያ ማቅረብ እንዲሁም፤ያሸነፉበትን ንብረት ዋጋ በሽያጭ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ስም CPO አዘጋጅተው በመክፈል ደረሰኝ መቀበል አለባቸው።

2.18.3 በጨረታው ማስታወቂያ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ ክፍያውን ያላጠናቀቀ አሸናፊ ተጫራች ለጨረታ ዋስትና ያስያዘውን ገንዘብ ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ ከጨረታው ይሰረዛል።

2.18.4 አሸናፊው ተጫራች ከሚረከበው ንብረት ውስጥ ጉድለት ቢገኝ ወይም ያሸነፈበትን ንብረት ሻጭ መስሪያ ቤት ሙሉ በሙሉ ሊያስረክበው ካልቻለ ጉዳዩን በፅሁፍ ለሻጭ መስሪያ ቤት የበላይ ሃላፊ ማቅረብና ውሳኔ ማግኘት አለበት። ሆኖም የሻጭ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ካልሠጠው አቤቱታውን ለመንግስት ግዠና ንበረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ በማቅረብ ውሳኔ ማግኘት ይችላል።

## 2.19 ከሻጭ መሰሪያ ቤት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት፤

2.19.1 ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተበትና ዋጋ ከተነበበት ቀን በኂላ የጨረታው አሸናፊና ተሸናፊ እስከሚለይበት ጊዜ ድረስ ከጨረታው ጋር

በተያያዘ ከመስሪያ ቤቱ የጨረታ ኮሚቴ ወይም ከጨረታ ጋር ተያይዞ ከሚሠራ ሠራተኞች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ አይቻልም፡፡

2.19.2 ተጫራቾች በማናቸውም የጨረታ ሂደት ላይ ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና ፣ በማጭበርበር ፣ በመመሳጠር ፣ በማስገደድና በማደናቀፍ ተግባር ተካፋይ መሆናቸው ከተረጋገጠ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡

# ክፍል 3 አጭበርባሪነት፣ሙስና እና አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት

## 3.1 የማጭበርበርና የሙስና ድርጊት

3.1.1 በአሸናፊነት የተመረጡ ተጫራቾች በራሳቸው ወይም በተወካያቸው አማካኝነት ጨረታውን ለማሸነፍ በማሰብ በሽያጭ ሂደቱ ውስጥ ከሚሳተፉ የሻጭ መ/ቤት ሠራተኞች እና የጨረታ ኮሚቴ አባላት ጋር የሙስናና የማጭበርበር ፣ የማሴር ፣ የማስገደድ ድርጊት በጨረታው ሒደት ወቅት ፈጽመው ከተገኙና ድርጊቱን መፈፀማቸው በማስረጃ ከተረጋገጠ አሸናፊነታቸው ውድቅ ተደርጎ በህግ እንዲጠየቁ ይደረጋል፡፡

3.1.2 ተጫራቾች በማናቸውም በጨረታ ሂደት ጊዜ ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና ፣ በማጭበርበር ፣ በመመሳጠር ፣ በማስገደድና በማደናቀፍ ተግባር ተካፋይ መሆናቸው ከተረጋገጠ በህግ እንዲጠየቁ ይደረጋል፡፡

3.1.3 ተጫራቾች የሙስናና የማጭበርበር ድርጊት የማይፈፅሙ ስለመሆናቸው ከዚሁ የጨረታ ሰነድ ላይ በተያያዘው ቅፅ ላይ ማመልከት ይኖርባቸዋል፡፡

## 3.2 አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት

3.2.1 በንብረት ሽያጭ አፈፃፀም ቅር የተሰኘ ተጫራች ለአቤቱታው መሰረት የሆነው የመጨረሻ ውሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በተከታታይ 5/አምስት/ የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በፅሁፍ በመጀመሪያ ማቅረብ ያለበት ለሽያጭ ፈፃሚው አካል የበላይ ሀላፊ ይሆናል ፡፡

**3.2.2** የሽያጭ ፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ በአስር(10) የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን አጣርቶ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3.2.3 ሆኖም የሻጭ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ካልሠጠው አቤቱታውን ለመንግስት ግዢና ንበረት አወጋገድ አቤቱታ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ በማቅረብ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

3.3.4 ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ በሁለቱም አካላት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል 4. የጨረታ ማቅረቢያ እና የውል ስምምነት ቅፆች

### 4.1. የጨረታ ማቅረቢያ ቅፅ

የሽጭ ፈፃሚ አክል -----------------(ሽያጭ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ)

የጨረታ ሰነድ የወጣበት ቀን-------- (የሽያጭ አወጋገድ ዘዴ)

የሽያጭ መለያ ቁጥር ------- -(መለያ ቁጥር ይፃፍ)

እኛ ከታች የፈረምነው ተጫራቾች / ተወዳዳሪዎች ከላይ የተጠቀሰውን የሽያጭ መለያ ቁጥር (መለያ ቁጥር አስገባ) የጨረታ ሰነዱን በተመለከተ የሚከተለውን እናረጋግጣለን ፡፡

የጨረታ ሰነዱን መርምረን ሁሉንም ያለምንም ተቃውሞ ተቀብለናል፡፡

በጨረታ ሰነዱ ፍላጎቶች መግለጫ ውስጥ የተዘረዘሩትን ዕቃዎችን እንዲሁም የመመለሻ ጊዜ ከጨረታ ሰነዶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እናቀርባለን ፡፡

ጨረታው ፀንቶ የሚቆየው በጨረታ ሰነዱ በተጠቀሰው የጨረታ ማቅረቢያው ማብቂያ የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ በፊት ምንጊዜም ቢሆን ውጤትና ተቀባይነት ይኖረዋል ፡፡ (የቀናቶች ብዛት በግልፅ ይቀመጥ)

ስም ፡ (በጨረታ ሰነዱ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ)

ኃላፊነት :(የፈራሚው ግለሰብ ህጋዊ አግባብነቱ የተመለከተው ግለሰብ ፊርማ ይግባ) (የተጫራቾች ሙሉ ስም ይግባ )

ቀን፡ -ቀን አስገባ ፣ ወር አስገባ ፣የተፈረመበት ዓ.ም ይግባ?

ሙሉ አድራሻ ----------------------------------

የስልክ ቁጥር-------------------------------------------------------

## 4.2. የፍላጎት መግለጫ

የሽያጭ መለያ ቁጥር-------------------------------------------

የሎት ቁጥር-----------------------------------------------

የሎት ስም------------------------------------------------------

| ምድብ | የዕቃው ዓይነት | የጨረታ ዋጋ/የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ | ተጫራቾች የሰጠው ዋጋ/የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |

ማሳሰቢያ

- ✓ ተጫራቾች የሚያቀርቡት የጨረታ የተጨማሪ እሴት ታክስን ያካተተ ነው
- ✓ ተጫራቾች በዚህ ጥቅል የተጠቀሱትን እቃዎች በሙሉ መጫራት የሚችሉ ሲሆን በጥቅል የሚወዳደሩበትን ዋጋ መጥቀስ ይኖርባቸዋል
- ✓ ተጫራቾች በሚሰጡት ዋጋ ላይ ስርዝ ድልዝ ካለው ተቀባይነት አይኖረውም

ስም------------

ፊርማ-------------

ቀን-----------------

## 4.3 የውል ስምምነት ቅፅ

የሽያጭ የሚፈፅመው (ዕቃው አይነት ይግባ)

የሽያጭ መለያ ቁጥር፤----------------------------------

ይህ ውል ዛሬ----------------------(ወር) ------------(ቀን) --------(ዓ.ም) (ከዚህ በኋላ"ገዥ" እየተባሉ የሚጠሩ) በሌላ በኩል በመሆን

- ✓ ሽያጭ ፈፃሚው አካል የተወሰኑ ዕቃዎችን(ዕቃዎቹ አጭር መግለጫ ይግባ) (ከዚህ በኋላ"ዕቃዎች" እየተባሉ የሚጠሩ) ለመሸጥ ጨረታ አውጥቶ ሻጩ ያቀረበው ጠቅላላ ዋጋ (የውል ዋጋ በፊደልና በአሃዝ ይግባ) (ከዚህ በታች "የውል ዋጋ" እየተባለ የሚጠራ)

ሁለቱ ወገኖች እንደሚከተለው ተዋውለዋል

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች በሻጭና በገዥ መካከል የመጨረሻ ፊራሚ ከፈረመበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ ይውላል፡፡

ዕቃው የሚገኝበት ቦታ------------------

የዕቃዎች ዝርዝርና የእያንዳንዱ ዋጋ---------------

ክፍያው የሚፈፀምበት ቀን

ፊርማ ---------------------(የሽያጭ ፈፃሚ መ/ቤት ስም)

ስለሻጭ ፈፃሚው አካል

(የሽያጭ ፈፃሚ መ/ቤት ስም ይግባ)

ፊርማ----------------(ፊርማ ይግባ)

ስም------------------(አግባብ ያለው ተወካይ ስም ይግባ)

ኋላፊነት----------------( ኋላፊነት ይግባ)

ቀን----------------------(ቀን ይግባ)

ገዥው

(የገዥው ስም ይግባ)

ፊርማ----------------(ፊርማ ይግባ)

ስም------------------(ሕጋዊ ውክልና ያለው ተወካይ ስም ይግባ)

ኃላፊነት----------------(ኃላፊነት ይግባ)

ቀን----------------------(ቀን ይግባ)

ምስክሮች

(የሽያጭ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ)

ፊርማ----------------(ፊርማ ይግባ)

ስም------------------(የምስክር ስም ይግባ)

ኂላፊነት----------------(ኂላፊነት ይግባ)

ቀን----------------------(ቀን ይግባ)

የገዥ ስም ይግባ

ፊርማ----------------(ፊርማ ይግባ)

ስም------------------(የምስክር ስም ይግባ)

ኂላፊነት----------------(ኂላፊነት ይግባ)

ቀን----------------------(ቀን ይግባ)

## ለሽያጭ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች  የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ

የ-----------------------------መ/ቤት የተሽከርካዎች ዝርዝር

ተሽከርካሪዎቹ  የሚገኙበት  ቦታ  ፡-  ---------------------------  በሚገኘው  የተቋሙ ግቢ ውስጥ

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪው አይነት | የተሽከርካሪው ኮድ | ሞዴል | የሞተር ቁጥር | የሻንሲ ቁጥር | የጨረታ መነሻ ዋጋ | ተጫራቹ የሰጠው ዋጋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | በአሃዝ | በፊደል |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

የተጫራቹ  ሙሉ  ስም-----------------------   ፊርማ--------------------   ቀን--------------

## ለሽያጭ  የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ያገለገሉ ንብረቶች የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ

የ--------------------------መ/ቤት የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝር

ንብረቱ የመገኝበት ቦታ------------------------------

| ተ.ቁ | የእቃው አይነት | መለያ ኮድ | መለኪያ | ብዛት | የጨረታ መነሻ ዋጋ | ተጫራቹ የሰጠው ዋጋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በአሀዝ | በፊደል |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |